# ልጅዎ መዋዕለ-ሕጻናት ገብቷል/ታለች

## ሥለ አምስት-ዓመት-ዕድሜዎች

5

ደስተኛው/ዋ የአራት ዓመት ልጅዎ አሁን አድጎ/ጋ ጸጥተኛና በቀላሉ የማይሸበር/የማትሸበር የአምሥት-ዓመት ልጅ ሆኗል/ሆናለች:: የአምስት-ዓመት-ልጆች በደንብ የሚግባቡ፣ ወሬ የሚያበዙ፣ እና ለአዋቂዎች ፍቅርና ውዴታ ያላችው ናቸው:: እርስዎን ለማስደሰት ይኳኋሉ፣ ነገር ግን ያደጉና ለትምህርት ቤት የደረሱ ልጆች ተደርገው ሊታሰብላቸው እንደሚገባ ይሰማቸዋል::

የአምስት-ዓመት-ልጆች በጽሁፍ የተቀመጡ ቃላት አንዳች ነገር የደሚናገር ትርጉም እንደሚኖራቸው ይገነዘባሉ:: ጥቂት ፊደላትንና ቃላትን ይለዩም ይሆናል፣ መጻፍና ማንበብም እንደሚችሉ ለማስመሰል ይሞካክራሉ:: ተርታ-ተረቶችም እንዲነበቡላቸውና እንዲተረኩላቸው ይወዳሉ:: በተለይም በጣም በርካታ ድርጊቶች፣ እንቅስቃሴዎችንና ድግግሞሽ ያሉባቸውን ተረቶች (ትረካዎች) ይወዳሉ::

የአምስት-ዓመት-ልጆች በራሳቸው ተነሳስተው ወደውጪ ለመውጣት ነጻነታቸውን ለመሞከር ይኳኋሉ፣ ሆኖም ግን ገደባቸው እስከምን ድረስ መሆን እንዳለበት ከቤት ሊነገራቸውና ይሄንኑም እንዲገነዘቡ አስፈላጊው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል:: የአምስት-ዓመት-ልጆች ለትምህርት ቤት እንደመዘጋጀት የመሳሰሉትን ጨምሮ የተለመዱ የየዕለት ድርጊቶችን ይፈልጋሉ:: ዕለተ-ቀኑን ከጥሩና ጤናማ ቁርስ ጋር አጣምሮ በተረጋጋና በተዝናና ጠዋት መጀመር በትምህርት ቤት ጥሩና አስደሳች ቀን እንዲውሉ ይረዳቸዋል:: ማታ ላይ ተስማሚውን ልብስ መርጦና አዘግጅቶ፣ እንደዚሁም ሳንድዊች ወይም ቁርስ የሚሆን ነገር አዘጋጅቶ ማደር የጠዋቱን የጊዜ መጣበብ ሊያቀለው ይችላል::

## በትምህርታቸው ውጤታማ ይሆኑ ዘንድ ልጆች ምን ዓይነት ልምድና ችሎታ ያስፈልጋቸዋል?

ስለልጆች ለትምህርት መድረስ ለምናስብ ሁሉ፣ የሚከተሉትን ሆነው እንዲገኙ ያስፈልጋል:

- በማህበራዊ ሁኔታ የተስተካከሉ፣ በስሜት የተረጋጉና በአካልም ጠንካራና ቀልጥፋ::
- ከአዋቂዎችና ከሌሎችም ጋር ለመግባባት የሚችሉ፣ በጽሁፍ በተቀመጡ አንዳንድ ሆሂያትና እያንዳንዳቸውም በቃል ከሚነገረው ድምጻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነትና ዝምድና መለየት (ለምሳሌ፣ "m" "መ" "mmmm" "መመመመ" የሚል ድምጽን ይሰጣል) እና ለተረቶች ፣ ለመጽሓፍትና ለምንባብ ፍላጎት ማሳየት::
- በቁጥርና ቁጥሩ በሚወክለው የብዛት መጠን መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ለይቶ ማወቅ መቻል፣ ፓተርኖችን (ዘርፎችን/ህረጎችን) መለየት (ለምሳሌ በስጋጃ ጠርዝ ላይ ያለን የቀለም ዓይነት አቀማምጥ በመደጋገም መናገር)፣ በምጽሐፍ ውስጥ ያሉ ወይም በአካባቢ የሚታዩ የቅርጽ ዓይነቶችን መልየት፣ (ለምሳሌ እንዳንድ ምልክቶች ባለአራት ማዕዘኖች ናቸው)፣ ነገሮችን በአንድ የተወሰነ አይነት ሥርዓት እየደረደሩ ማስቀመጥ መቻል (ለምሳሌ ከትልልቅ ወደ ትንንሽ ባለ ሥርዓታዊ አቀማመጥ)::
- አካባቢያቸውን ማወቅ/ጎረቤቶችን፣ እንስሳትን፣ እጽዋትን፣ እንደዚሁም ሰዎች በቤተሰባቸውና በማህበረሰቡ (ኮሚዩኒት) ውስጥ ያላቸውን ሚና ለይቶ ማወቅ::
- በግል የፈጠራ ስራ መደሰትና መዝናናት እና በጥበባት አማክኝነት በራስ ፈጠራ ራስን መግለጽ መቻልን ማድነቅ (ለምሳሌ ይሄንን ልስራ ብሎ በጭንቅላት አሰላስሎ መስራት፣ ሸክላን፣ የቅብ ቀልምን፣ ማርክሮችን፣ ወዘተ በመጠቀም)::

የመዋዕለ-ሕጻናት አስተማሪዎች፣ ወደ መዋዕለ-ሕጻናት አዲስ በሚገቡ ልጆች ላይ ሊንጸባረቁ ይችላሉ ተብለው በሚጠበቁ አመልካቾች ላይ በመመስረት፣ በመጀመሪያዎቹ ጥቂት የትምህርት ቀናት ውስጥ የእያንዳንዱን ልጅ ዘዴና ችሎታ ይገመግማሉ:: አስተማሪዎቹ የነዚህን ሰባት የዕድገት ሁኔታዎች ልክና መጠን የሚመለከት ኢንፎርሜሽን ያቀርባሉ፡ የግለ-ሰብዓዊና ማህበረሰባዊ እድገት፣ ቋንቋና የመጻፍ-ማንበብ ችህሎታ፣ ሥሌታዊ (ሂሳባዊ) አስተሳሰብ፣ ሳይንሳዊ እስተሳሰብ፣ ህብረት ትምህርት፣ ሥነ-ጥበብ፣ እና አካላዊ እድገትና ጤና:: እባከዎ በመኸር እንዲደረግ በታቀደው የወላጅ-አስተማሪዎች ጉባዔ ላይ ተገኝተው የልጅዎን ውጤት በሚመለከት ከልጅዎ አስተማሪ ጋር ይወያዩ::



Amharic

## የልጅዎን በመዋዕለ-ሕጻናት የመማር ሁኔታ ለማገዝ ማበረታታት ከሚያደርጓቸው ጥቂት ነገሮች የሚከተሉትን የሚጨምሩ ሲሆን በነዚህ ላይ ብቻ የተገደቡ ግን አይደሉም፤

### ግለ-ሰብዓዊና ማህበረሰባዊ እድገት

- ለሣምንት የሚሆን ዕቅድ ያዘጋጁ:: ከተለመዱት የዕለት-ከዕለት ተግባራተዎ ውጪ ሊሆኑ የሚችሉትን ማንኛቸውንም ጉዳዮች በተለዩ አቅላማት በማቅለምና በማስመር ልጅዎ የሳምንታዊ የጊዜና የድርጊቶች ሰሌዳን በማዘጋጀት (በማቀድ) እንዲረዳዎት ያድርጉ:: ይህን ማድረጉ ደግሞ የነገሮችን ሥርዓታዊና እለፍ-ተቀደማዊ አቀማመጦችን እንዲገነዘብ ያደርገዋል፤ ከዚያም የሚቀጥለው የድርጊት ወይም የጊዜ ሰሌዳው ምን እንደሆነ እንዲያውቀው መተማመኛ ይሆንለታል::

- የምርጫ ዕድል ሥለመስጠት:: ልጅዎ የሆነ ነገር እንዲመርጥ ወይም በሆነ ነገር ላይ እንዲወስን ሲያደርጉ፤ ለምሣሌ÷ የመኝታው ወቅት ሲደርስ የሚያነበውን ተረት በመምረጥ፤ ወይም ለዘመድ ወይም ለጓደኛ የሚሰጥ የልደት ካርድን በመምረጥ ጊዜ፤ የመምረጥ ነጻነቱን እንዲጠቀም ያበረታትቱት::

### ቋንቋና መጻፍ-ማንበብ

- ከቃላት ጋር ይጫዎተ:: የልጅዎን የመጀመሪያ ሥም በመጠቀም የሥም-የሥም ጨዋታ ይጫወቱ፤ ከዚያም ከስሟ የመጀመሪያው ፊደል (ሆሄ) ድምጽ ጋር ተመሳስይነት ያላቸውን ቃላት እንዲታስብና እንድትለያቸውም ይርዷት:: መዝሙር ለመዘመር፤ ግጥሞችን ለማሰማት፤ እና የቤት መምቻዎችን ለመደርደር አጋጣሚዎችን ይፈልጉ::

- የቃላት-ካርድ ማህደር (ፋይል) ያዘጋጁ:: ልጅዎ ለማንበብ የሚፈልጋቸውን ቃላት ይጻፉ፤ አንድ ቃል በየአንዳንዱ ካርድ ላይ ይጻፉ፤ ከዚያም አዳዲስ ቃላትን እየተማረ በሄደ ቁጥር እርሰዎም አዳዲስ ካርዶችን እየጨመሩ ይሂዱ:: አንድ ቃልን ለመጻፍ ወይም የአንድን ልዩ ዓይነት ቃል ድምጽ ለመለማመድ ሲፈልግ ካርዶቹን ከቃላቱ ማህደር እንዲመርጥ ያበረታቱቱ::

- የቃል ጽሁፍን ይጠቀሙ:: ልጅዎ የምትነግረዎትን ቃላት በመጻፍ ልጅዎ በምትስራቸው ሥዕሎች ላይ ተረት ለመጨመር ዕድሉን ይጠቀሙበት:: ቃላቱን እየጻፉ ሳለም የፊደላቱን (ሆሄያቱን) ድምጸት እርሰዎ ሲናገሯቸው እንድትስማ ያድርጉ፤ ይህ ሁኔታ በንግግርና በጽሁፍ ቋንቋ መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲታይና እንድታስተውል ያደርጋታል:: ተረቶችን መናገር ተረትን ለመጻፍ በጣም ጠቃሚው የመጀመሪያው ደረጃ ነው::

- ተሳትፎ ያድርጉ:: ከንባቡ በኋላ፤ ከታሪኩ ገጸ-ባህሪያት አንዱ እንደሆኑ አድርገው ያስመስሉ፤ ከዚያም ልጅዎ ራሱም አብረውት ያነበቧቸውን ትረካዎች በድርጊት እንዲተውናቸው ያበረታቱት:: ድርሻዎን በተነቃቃ ስሜት ይጫወቱት:: የገጸ-ባህሪውን ቃላት በድምጸተ-ዓጽንዖት መድገም ወደኋላ ላይ ልጅዎ እራሱን ችሎ ማንበብ ሲጀምር አንደበተ-ርቱዕ እንዲሆን ያበረታታዋል::

### ሥሌታዊ (ሂሳባዊ) አስተሳሰብ

- ከልጅዎ ጋር በመሆን አንዳንድ ነገሮችን ይሰብስቡ:: የነገሮችን ጥርቅም (ቡድን)፤ ለምሳሌ እንደ የእቃ መያዣ ክዳኖችን፤ ቁልፎችን (አዝራሮችን)፤ የቁልፍ መያዣ ሰንሰለቶችን ይሰብስቡ፤ ከዚያም እርሰዎና ልጅዎ በተስማማችሁበት አንድ ደንብ መሰረት ነገሮቹን (ለምሳሌ፤ ትልልቆቹን ከትንንሾቹ፤ ግጣሞቹን ከምግብ መያዣዎቹ፤ እና ግጣሞቹን ከመጠጥ መያዣዎቹ) በመለየት በመልክ-በመልካቸው አስቀምጧቸው::

- ዘርፎችንና ሀርጎችን አብጠርጥረው የሚለዩ ይሁኑ:: በአልባሳት፤ በግድግዳ ወረቀቶች፤ መመገቢያ ቁሳቁሶች፤ በስጋጃ ምንጣፍ ላይ የሚታዩ ዘርፎችንና ሀረጎችን ለማግኘት በዓይነዎ ያድኑ::

- መቁጠረዎን ይቀጥሉ:: በቤት አካባቢ ከልጅዎ ጋር ስራ በመስራት ላይ እንዳሉ፤ ሲያጥቡ የካልሲዎቹን ቁጥር፤ እራት ሲያዘጋጁ ደግሞ የድንቾቹን ቅቁጥር ጮኽ ብለው ይቁጠሩ:: አንዳንድ ለምሳሌ፤ "እያንዳንዳችችን ከሾርባችን ጋር ሁለት-ሁለት ብስኩት እንዲኖረን ስንት ብስኩቶች ያስፈልጉናል?" የሚሉትን ዓይነት ፕሮብሌሞች ያቃልሉ::

- የቅርጽ ዓይነቶችን ከልጅዎ ጋር በመሆን ይፈልጉ:: በቤት ውስጥ ሊያገኟቸው የሚችሏቸውን ወይም ወደሱቆች ወጣ ባሉበት ጊዜ ሁሉ፤ ሁሉንም የቅርጽ ዓይነቶች (ባለሦሥት-ጎን፤ ክብ፤ ባለ-አራት ጎን፤ ወዘተ) ይመልከቱ፤ ያፈላልጉ::

### ሳይንሳዊ አስተሳሰብ

- ልክ እንደ ሳይንቲስት ሁሉ ስሜቶቸዎን ይጠቀሙ:: ልጅዎ በአካባቢው ያሉትን ነግሮች ሁሉ፤ እንዲመለከት፤ እንዲያሸት፤ እንዲያዳምጥና እንዲዳስሳቸው ያበረታቱት:: ዛፎችና ጫካ ባለበት አካባቢ በእግር ጉዞ ይዘውት እየተንቀሳቀሱ እርሰዎ ስለሚነኳቸው፤ ስለሚያሸቷቸው፤ ስለሚያዩአቸውና ስለሚሰሟቸው ነገሮች ያውሩለት::

- ከልጅዎ ጋር ሆነው ይገረሙ (ይደነቁ):: ስለሚከነክኑዎት ወይም በጣም ተፍጥሯዊ ምስጢራቸው ስለሚያስገርሙዎትና ስለሚያስደንቁዎት ነገሮች "ለምሳሌ፤ ከአትክልት ማጠጫው ቧንቧ ከሚንጠባጠበው ዕንባ ዓይነት ውኃ ቀስተ-ደመና ሊታይ የመቻሉ ነገር በጣም ይገርመኛል!" በማለት ሲገረሙና ሲደነቁ ልጅዎ እንዲሰማዎት ያድርጉ:: ልጅዎን "እንዴት አወቅህ?" ወይም "ለምን ይመስልሃል፤ እስቲ ንገረኝ" የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት ማብራሪያውን ይጠይቁት:: ዶክተረዎን፤ የቧንቧ ጠጋኙን፤ የቴሌሁሻዥን መሃንዲሱን የመሳሰሉ ሰዎች ልጅዎ ሊረዳቸው ለሚችላቸው ጥያቄዎች ማብራሪያ እንዲሰጡት ያበረታቷቸው::

### ሕብረት ትምህርት

- ለተለያዩ ቦታዎች የተለያዩ ደንቦች:: የምንከተላቸው የባህሪ ዕይነቶች፤ እንደቦታዎቹ ዓይነትና ሁኔታ (ለምሳሌ፤ ጸባይ (ባሕሪ) በቲያትር ቤት፤ ጸባይ (ባሕሪ) በኳስ ጨዋታ ቦታ) ሊለያዩ እንደሚችሉ ከልጅዎ ጋር ያውሩ::

- በማህበረሰቡ ውስጥ አገልግሎት ስለሚሰጡት ያንሱ:: ቤተሰበዎን የሚረዱትን ሰዎች ሚና፤ ለምሳሌም የቆሻሻ ሰብሳቢዎችን፤ የፖስታ አመላላሽ ተቀጣሪዎችን፤ የግሮሰሪ ሱቅ ሻጮችን፤ እያነሱ ከልጅዎ ጋር ያውሩት::

### ሥነ-ጥበብ

- ፈጠራን ያስፋፉ (ያበረታቱ):: የስነ-ጥበበ መሳሪያዎች (ከለሮች፤ ማርከሮች፤ ወረቀት፤ መቀሶች) በቅርበዎ እንደሚገኙ አድርገው ያሰባስቡ፤ ከዚያም ልጅዎ ሃሳቦቹንና ስሜቶቹን በጥበባዊ የፈጠራ ዘዴ እንዲገልጻቸው ያበረታቱት:: ("ስለሳልከው ስዕል እስቲ ንገረኝ") በማለት ስለፈጠራ ስራዎቹ እንዲያወራ ያበረታቱት:: አሻንጉሊቶች እና ብሎኮችንና የግንባታ አሻንጉሊት የመሳሰሉትን የግንባታ ስራ ቁሳቁሶች ያቅርቡለት::

- ሙዚቃ እየዘፈኑ እብረው ይደሰቱ:: በመኪና ውስጥ እያላችሁ ይዝፈኑላት (ይዘምሩላት)፤ መሳሪያ ያዘጋጁ፤ ምቱን በጭብጨባ ያጅቡት፤ ይደንሱ፤ በሬኮርድ የተዘጋጁ በርካታ የተለያዩ ሙዚቃዎችን ያጫውቱ፤ ከዚያም ስለተለያዩ ሙዚቃዎች ድምጾች ያውሩ:: ወደትርዒት ወይም የሙዚቃ ትርዒት ቦታ ሄደው ይመልከቱ::

### አካላዊ እድገትና ጤና

- እንቅስቃሴን ያበረታቱ:: ከጎረቤት፤ ከግቢዎ ውስጥ፤ በፓርክ አካባቢ፤ ወይም በተዘጋጀና በተቀነባበረ ስፖርታዊ ወይም እንቅስስቃሴያዊ ፕሮግራም እየሄደች በየቀኑ እንዲትጫወት እድል (ፋታ) ይስጧት::

- ልጅዎን የሚረዱበትን መንገዶች ያዘጋጁ:: ለምሳሌ አትክልትና ፍራፍሬዎችን እንደመላጥ፤ ጭማቂ እንደመቅዳት፤ የተከፈተ እንቁላልን እንደመምታት፤ እና የፍራፍሬ ዱቄት መበጥበጥን የመሳሰሉ በእጁ ተጠቅሞ ሊሰራቸው የሚችል የዘወትር ስራዎችን እንዲሰራ ይጠይቁት::